# ከፓርላማው በስተጀርባ የነበረው የአቶ ተመስገን ዘውዴ ገመና

(ከአብዱራህማን አህመዲን፣ የቀድሞ የፓርላማ አባል)
Email: ahayder2000@gmail.com

*(ይህ ጽሑፍ ዛሬ ታህሳስ 26 - ጥር 3 ቀን 2006 በወጣው ሎሚ መጽሔት ላይ ታትሟል፡፡ መጽሔቱን የማያገኙ፣ በተለይም በውጭ ሀገር ያሉ ዜጎች ሁሉ ቢያነቡት 'ይጠቅማል' በሚል መንፈስ በዚህ ድረ-ገጽ ላይ እንዲታተም ተልኳል፡፡)*

በ1997 ዓ.ም በተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ የያኔውን ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን/ቅንጅት ፓርቲን ወክለው፣ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 5 የምርጫ ክልል ተወዳድረው በማሸነፋቸው የ3ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የነበሩትን የተከበሩ አቶ ተመስገን ዘውዴን የሕይወት "ታሪክ" እና የፖለቲካ "ቁጭት" የያዘ መጽሐፍ "ከፓርላማው በስተጀርባ" በሚል ርዕስ ታትሞ ሰሞኑን በገበያ ላይ ውሏል፡፡

ይህ መጽሐፍ የተሰናዳው ዳንኤል ተፈራ በተባለ (አንተ ያልኩት ያው በተለምዶ ጋዜጠኛና ደራሲ 'አንተ' ስለሚባል ነው) ግለሰብ ነው፡፡ ካልተሳሳትኩ አቶ ዳንኤል ከዚህ ቀደም የዶ/ር ነጋሦ ጊዳዳን የሕይወት ታሪክ የያዘ መጽሐፍ "የነጋሦ መንገድ" በሚል ርዕስ አሰናድቶ ማሳተሙ ይታወሳል፡፡ ይህ ሁለተኛ መጽሐፉ መሆኑ ነው፡፡ በነካ እጁ ሦስት፣ አራት፣... እያለ እንደሚቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

"ጋዜጠኛ" ዳንኤል (አሁን ፖለቲከኛም ሆኗል ሲባል ሰምቻለሁ) የጀመረው የታዋቂ ግለሰቦችን የሕይወት ታሪክ (ባዮግራፊ) ቃለ ምልልስ አድርጎ የማቀነባበር ዘዴ ሌሎችም እየተከተሉት ያለ የሚበረታታ አሰራር ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ አቶ ዳንኤል "በፖለቲከኛነት" እና "በጋዜጠኛነት" መሀል ላይ ቆሞ ከሚመናተል አንዱን አቅጣጫ ቢመርጥ የተሻለ መስሎ ታይቶኛል፡፡ ምክንያቱም ጋዜጠኛነት ገለልተኛነትን ይጠይቃል፡፡ ፖለቲካው ደግሞ ወገንተኛነትን ይጠይቃልና ነው፡፡

አቶ ዳንኤል የአቶ ተመስገን ዘውዴን ታሪክ ባቀነባበረበት በዚሁ መጽሐፉ በገጽ 92 ላይ እንዲህ የሚል ሃሳብ አስፍሯል፣ "የየትውልዱን ሀቀኛ ታሪክ ሳይበረዝ ልናስተላልፍ የምንችለው ከባለታሪኮች አፍ በመስማት ይመስለኛል" ይላል፡፡ በዚህ አባባል መስማማት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከባለ ታሪክ አፍ የተነገረ ሁሉ "ሀቀኛ" ታሪክ ሊሆን አይችልም፡፡ አንድ ታሪክ "ሀቀኛ ታሪክ" ሊሆን የሚችለው ባለታሪኮቹ ለነፍሳቸውም ለስጋቸውም አድረው፣ ያዩትን፣ የሰሙትንና የሆነውን ሳይቀንሱ፣ ሳይጨምሩና ሳይበርዙ የተናገሩት እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ያ ካልሆነ ታሪኩ "የውሸት ታሪክ" ነው የሚሆን!

ታሪክን የሰሚሩትም ሆኑ የሚተርኩት ሰዎች ናቸው፡፡ ከሰዎች ውስጥ ደግሞ አንዳንዶቹ ሰው በመሆናቸው የሰው ባህሪ የሆነው ከሀቅ የመሸሽ እና ከእውነት የመራቅ ዝንባሌ ይታይባቸዋል፡፡ ይህንን ዝንባሌ በማረቅ ማስተካከል የሚቻለው ደግሞ ከፖለቲካ ወገንተኛነት በራቀ መንፈስ ድርሳናትን የሚያትቱ ሀቀኛ ጸሐፊዎች ናቸው፡፡ ዛሬ በየስፍራው ያሉ ዕድሜ ጠገብ የታሪክ ሰነዶቻችን ተዓማኒነት አጥተው በታሪክ ምሁራን

ዘንድ "የደብተራ ታሪክ" የሚል ስም የተሰጣቸው፤ በማሞገስና በማወደስ የተሞሸሩ፣ በውሸትና በማጋነን ላይ የተመሰረቱ፣ የአንድ ወገን የትረካ ውጤት በመሆናቸው ይመስለኛል፡፡

አቶ ዳንኤል የአቶ ተመስገንን የሕይወት ታሪክ ሲያዘጋጅ እሳቸው ያሉትን ነገር ሁሉ እንደ ወረደ በመጻፉ፤ ጊዜና ጉልበት ያባከነበትን መጽሐፍ በሕጸጽ የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ አቶ ዳንኤል የሚያዘጋጀው የታሪክ መጽሐፍ መሆኑን ነግሮናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ አቶ ተመስገን ስለሚናገሩት ነገር እውነት መሆን ወይም አለመሆን ጭራሽ ያሰበው አልመሰለኝም፡፡ ከዚህ በፊት አቶ ዳንኤል ባሳተመው መጽሐፍ ዶ/ር ነጋሦ ስለማያውቁት ነገር መናገራቸውን ያዩ አንዳንድ ሰዎች በጋዜጦች ላይ አስተያየት ማቅረባቸውን አስታውሳለሁ፡፡

አቶ ዳንኤል፤ አቶ ተመስገን ስማቸውን እያነሱ አስተያየት የሰጡባቸውን ሰዎች (ሁሉንም ባይሆንም) የተወሰኑትን አግኝቶ "እከሌ እንዲህ የሚል ሃሳብ ተናግሯል፣ ይህ ነገር እውነት ነው ወይ?" የሚል ጥያቄ በማቅረብ የተሟላ ሰነድ ቢያዘጋጅ የተሻለ ይሆን ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡ ያን ቢያደርግ ኖሮ፤ እኔንም ይህቺን ማስታወሻ ከማዘጋጀት ያድነኝ ነበር፡፡ ለዛሬው ለመጽሐፉ አዘጋጅ ሳይሆን የውሸት ታሪክ በመናገር የመጽሐፉን አዘጋጅና አንባብያንን ላሳሳቱት ለአቶ ተመስገን ዘውዴ የሚከተለውን መልስ አቀርባለሁ፡፡

የተከበሩ አቶ ተመስገን ዘወዴ "የሕይወት ታሪኬ ነው" ብለው የተረኩትን መጽሐፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አንብቤዋለሁ፡፡ በገጽ 150 ላይ አቶ ተመስገን እንዲህ ይላሉ **"በእውነት ፊት ቆሜ ለትውልዱ ማስተላለፍ በምፈልገው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መዋሸት አልፈልግም"** ይላሉ፡፡ ውድ አቶ ተመስገን! **"መዋሸት አልፈልግም"** ማለትን ምን አመጣው? ነገሩ "የገብርኤልን መገበሪያ የበላ..." መሆኑ ነው፡፡ ቃልና ተግባራቸው ለየቅል የሆነው አቶ ተመስገን እንዲህ ያለ መሀላ ቢደረድሩም በተለይ እኔን በተመለከተ ስሜን ጠቅሰው ነጭ ውሸት መተረካቸውን አንብቤአለሁ፡፡ በሌሎች እኔም በማውቃቸው ጉዳዮች ላይም እንዲሁ የተሳሳተ፣ ከመጠን በላይ የተጋነነ እና "ሳይሆን አይቀርም" በሚል ጥርጣሬ ላይ ተመስርተው ሃሳብ መሰንዘራቸውን አስተውያለሁ፡፡ ሊታረሙ ይገባቸዋል የምላቸው ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም የጋዜጣውን ዐርብ ላለማጣበብ ዋና ዋና በምላቸው ላይ ብቻ ማተኮርን መርጫለሁ፡፡

ቅድሚያ ሰጥቼ የማነሳው የእኔና የአቶ ተመስገንን ፀብ በተመለከተ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አቶ ተመስገን ትንሽ እውነት ይዘው በርካታ ውሸትና ተረት ነው የተናገሩት፡፡ መጣላታችን፣ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ሊደበድቡኝ መወራጨታቸው፣ በዚህም ምክንያት እኔ ክስ ማቅረቤና ሽማግሌ ልከው መታረቃችን እውነት ነው፡፡ ከዚያ ውጪ ያለው የፈጠራ ተረት ነው፡፡ የእርሳቸውን ሃሳብ እየጠቀስኩ ላብራራ፡፡

የጠቡን መነሻና ሂደት በተመለከተ እንዲህ ይላሉ አቶ ተመስገን፤ **"...አንድ ቀን የአማካሪ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ከመሬት ተነስቶ 'አቶ ተመስገን እኛ እኮ ነን ፖለቲካ ያስተማርንህ' አለኝ... ስንወጣ ተከተልኩና 'አንተ! እንዴት ነው እኔን ፖለቲካ ልታስተምረኝ የምትችለው?' አልኩት... ፈጠን እያለ ሰምቶ ያልሰማ በመምሰል ከእኔ እየራቀ ሄደ፡፡ በሌላ ቀን እኔ ወደ ፓርላማ ስገባ እሱ ደግሞ ሲወጣ ተገጣጠምን፡፡ እኔ መጣላታችንን ረስቼው ሰላም ልለው ሲቃጣኝ 'በህግ አምላክ! እንዳትጠጋኝ! ሊደበድበኝ ነው' ብሎ ጮኸ፡፡ ... ሚጢጢ ሴራ እንደሆነች ለመገመት ብዙ አልፈጀብኝም..."** (ገጽ 207-208)

ወንድሜ አቶ ተመስገን ሆይ! አሁን ሁሉም ነገር አልፏል፡፡ እኔና እርስዎም ታርቀን ከዚያ በኋላ በሰላም ብዙ አሳልፈናል፡፡ ፓርላማውንም ለቀናል፡፡ እኔማ ፖለቲካውንም ለቅቄ የእፎይታ ኑሮ መኖር ከጀመርኩ እነሆ አራት ዓመት መሆኑ ነው፡፡ ታዲያ አሁን እንዲህ ያለውን ተራና የማይረባ ጉዳይ እንደ ትልቅ ነገር በመጽሐፍ እንዲታተም ማድረግ ምን ፋይዳ አለው? ለአንባቢውስ ምን ያስተምራል? ምን ዓይነት የፖለቲካ ትርፍስ ያስገኛል?

ውድ አቶ ተመስገን! እዚያ ቅንጅት የሚባል ስብስብ ውስጥ የነበራችሁ ሰዎች አንዲት ተራ የብልጠት መንገድ አለቻችሁ፡፡ ከሰረቀ በኋላ "ሌባ! ሌባ!" እያለ እንደሚሮጠው የመርካቶ ጮሌ፤ አንድ መሆን የማይገባው ስህተት ራሳችሁ ትሳሳቱና በነገሩ በሌለበት የዋህ ላይ ሀጢያቱን ለማላከክ "ያዘው!... እሱ ነው!... ከእነከሌ ጋር ሆኖ እያሴረ ነው!" ወዘተ. እያላችሁ በማዋከብ የየዋሃንን ቀልብ ለመሳብ የማትወጡት ተራራ የማትወርዱት ቁልቁለት የለም፡፡ እንዲህ ያለው የተባነነበት የብልጣብልጥ መንገድ ጊዜአዊ እርካታን ያስገኝ እንደሆነ እንጂ ዘላቂ ውጤት አያመጣም፡፡ ሐቁ ገሃድ ሲወጣ እርቃናችሁን መቅረታችሁ ተደጋግሞ ታይቷል፡፡ ይህ የተነቃበት ታክቲክ ለጊዜው ለመጽሐፍ ማሻሻጫ ይሆን ይሆናል፡፡ አቶ ተመስገን በዚህ መልኩ ውሸት ያቀረቡት እኔ ከፖለቲካው መድረክ ስጠፋ ከምድረ-ገጽ የጠፋሁ መስሎአቸው ከሆነ አሁንም የባሰ ስህተት ነው የሚሆን፡፡

ነገሩ ከተነሳ አይቀር የተሳሳተውን ለማረቅ ይቻል ዘንድ በዚያ እለት የሆነው እንዲህ ነው፡፡ በስብሰባው ላይ "**አቶ ተመስገን እኛ እኮ ነን ፖለቲካ ያስተማርንህ**" ያልኩት ከመሬት ተነስቼ አልነበረም፡፡ አቶ ተመስገን "**ኢዴፓ የሚባል ፓርቲ የለም፡፡ በውህደት ከስሟል**" በማለት የመጀመሪያዋን ጠጠር ወረወሩ፡፡ እኔ የመናገር እድል ሲሰጠኝ ደግሞ "**የለም አቶ ተመስገን ኢዴፓ አልከሰመም፡፡ እርስዎ ራስዎ እዚህ የተገኙት በኢዴፓ ነው፡፡ እርስዎ የግል እጩ ተወዳዳሪ ነበሩ፡፡ እኛ ወደ ኢዴፓ አምጥተን፣ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለማችንን አስተምረን፣ በኢዴፓ ስም አወዳድረን፣ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን በቅስቀሳና በታዛቢነት እንዲያግዙዎት ባናደርግ ኖሮ እንደ ሌሎቹ የግል ተወዳዳሪዎች እርስዎም አይመረጡም ነበር፡፡ እዚህ ቦታም ላይ አይገኙም ነበር...**" የሚል መንፈስ ያለው ሃሳብ ነበር የተናገርኩት፡፡ ኢዴፓን ወክዬ እዚያ ቦታ ላይ እስካለሁ ድረስ ይህንን የመናገር ግዴታ ነበረብኝ፡፡ ደግሞም የተናገርኩት አንድም ስህተት አልነበረውም፡፡

አቶ ተመስገን ፖለቲካ ቢያውቁ ኖሮ፣ አቶ ተመስገን ስለዴሞክራሲ የጠራ ግንዛቤ ቢኖራቸው ኖሮ፣ አቶ ተመስገን የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ቢገባቸው ኖሮ፣... እኔ "**ፖለቲካ አስተማርኩህ**" ብላቸው እንኳ ሃሳቤን በሃሳብ ለማሸነፍ እዚያው መድረክ ላይ ይከራከሩ ነበር እንጂ በቡጢ ካልነረትኩህ ብለው በተደጋጋሚ ለድብድብ አይጋበዙም ነበር፡፡ እንዲያው ለነገሩ "**ፖለቲካ ያስተማርንህ እኛ ነን**" ማለትስ ያን ያህን ደምን የሚያፈላ ሆኖ ለዱላና ለድብድብ የሚጋብዝ ነገር ነው? ይሄ ነው እንግዲህ የአቶ ተመስገን የፖለቲካ ብስለት!

አቶ ተመስገን በመጀመሪያው ቀን እየተሳደቡ ሲከተሉኝ ሸሸሁት፡፡ በወቅቱ ግን አቶ አብዱረሂም ያሲን የተባሉ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመጡ የኮሚቴአችን አባል አብረውን ስለነበሩ "ይሄን ሁኔታ ልብ አድርጉልኝ" አልኩና አለፍኩት፡፡ ....እኔ ነገሩ እለታዊ ግጭት መስሎኝ ትቼው ነበር፡፡ በሃሳብ መሸነፉ ያንገበገባቸው አቶ ተመስገን ግን ሳምንት ባልሞላ ጊዜ አሁንም ቡጢያቸውን አሳምረው ሊነርቱኝ ከእሳቸው በማይጠበቅ ሁኔታ እየተሳደቡ ሲከተሉኝ በወቅቱ በጥበቃ ላይ ወደነበሩት ፖሊሶች እያመለከትኩ "በህግ አምላክ" እያልኩ ሸሸሁ፡፡ ፖሊሶቹም እዚያ የተቀመጡት የእኛኑ ደህንነት ለመጠበቅ

በመሆኑ አቶ ተመስገንን 'ተው' ብለው እንዳይመቱኝ ሲከላከሉ አቶ ተመስገን እነሱን ጭምር ይሰድቧቸውና ይዘልፏቸው ጀመር፡፡

ከዚያ በላይ መታገስ ሕይወቴን አደጋ ላይ እንደሚጥል ስለገመትኩ በምክር ቤቱ ደንብ መሰረት ከሰስኩ፡፡ ታዲያ ይሄ ምነድነው ጥፋቱ? አቶ ተመስገን ራሱ ተማቶ ራሱ እንደሚጮኸው ጅራፍ፣ ምንም ሳልደርስባቸው ካልተማታሁ አሉ፣ ስከስ ደግሞ ከኢህአዴግ ጋር ተመሳጥሮ ከሰሰኝ ይላሉ፡፡ አሁን ይሄ አባባል የጤና ነው? ወይስ 'እኔ ብፈልግ ልስደብህ፣ ላዋርድህ፣ አለፍ ሲልም በቡጢ ላደባይህ፣ አንተ አንገትህን ደፍተህ ሁሉንም ነገር አንገትህን ደፍተህ መቀበል ነበረብህ' ነው የሚሉት አቶ ተመስገን? ሽማግሌ ልከው የታረቅነው እኮ እኔ ጥፋተኛ ስለሆንኩ አደለም፡፡ ከዚህ በላይ የምለው የለም፡፡ ሁሉንም ነገር አንባቢ ይፍረደው!!!

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሦስት ነገሮችን በታሪክ ፊት መናገር እፈልጋለሁ፡፡ (1ኛ) እንኳን ከእኔ ጋር ሴራ ሊያቀነባብር አቶ ተመስገንን በእኔ ክስ ምክንያት ከም/ቤት እንዳይባረሩ ያደረገው ኢህአዴግ ነው፡፡ መጽሐፉ ላይ እንደተጠቀሰው አቶ ተመስገን እኔን ይቅርታ እንዲጠይቁ አቅጣጫውን ያመላከቷቸው፣ መላውን የነገሯቸው የኢህአዴግ አባል ናቸው፡፡ እኔን ደግሞ አንድ የኢህአዴግ ከፍተኛ ሰው ጠሩኝና በክሱ ላይ አክርሬ ብሄድ ለምክር ቤቱ፣ ለአቶ ተመስገን፣ ለተቃዋሚው ጎራም ሆነ ለመረጠን ሕዝብ ጭምር ጥሩ እንዳልሆነ በመግለጽ ነገሩን ረጋ ብዬ እንዳየው መከሩኝ፡፡ የእኔም ፍላጎት አቶ ተመስገን ከፓርላማ እንዲባረሩ ለማድረግ ባለመሆኑ ክሴንም ሳላነሳ፣ እርቁንም እምቢ ሳልል በእንጥልጥል ተውኩት፡፡ ክሱን ያላነሳሁት የአቶ ተመስገን ባህሪ አስቸጋሪ በመሆኑ ሌላ ጊዜ እቀብጣለሁ ቢሉ የመጨረሻዋን ካርድ ለመምዘዝ እንዲያመቸኝ በማሰብ ነው፡፡

(2ኛ) አቶ ተመስገን ተደጋጋሚ የድብድብ "ግብግ" ሲያቀርቡልኝ መሸሽን የመረጥኩት ደካማና አቅመቢስ ስለሆንኩ አልነበረም፡፡ እንኳን እንደ አቶ ተመስገን ያለ ጉድጓዱ የተማሰ፣ ልጡ የተራሰ ሰው ጋር ከዕድሜ እኩዮቼም ጋር ቢሆን እራሴን ከጥቃት ለመከላከል የሚያስችል አፍላ የወጣትነት ጉልበት እንዳለኝ አምናለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ አንደኛ፡- እኔ የወጣሁበት ማህበረሰብም ሆነ በመልካም ስነ-ምግባር ኮትኩቶ ያሳደገኝ ቤተሰቤ እንኳን በእድሜ ከሚበልጠኝ አዛውንት ከእድሜ እኩዮቼም ጋር ቢሆን ግጭትን በድብድብ እንድፈታ ስላላስተማረኝ፣ ሁለተኛ፡- በነበረኝ የፖለቲካ ሕይወትም እከተለው የነበረው መርህ ግጭትን በውይይት በመፍታት ላይ የተመሰረተ ስለነበር፣ ሦስተኛ፡- አቶ ተመስገን ጋር መደባደብ አቶ ተመስገንን ጀግና (Hero) ማድረግ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት፣ አራተኛ፡- በግለሰባዊ ሕይወቴም በሕግ የበላይነት የማምንና ለሰላማዊ አማራጭ የቅድሚያ ቅድሚያ የምሰጥ በመሆኑ፣ የአቶ ተመስገንን የድብድብ ትንኮሳዎች በመሸሽ ማሳለፍን እንድመርጥ አስገድዶኛል፡፡

(3ኛ) አቶ ተመስገን ስማቸውን እያነሱ ከወቀሷቸው ሰዎች አንዱ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ የነበሩት አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ናቸው፡፡ አቶ ተመስገን አላወቁትም እንጂ አምስት ዓመት ሙሉ መድረክ ሰጥተው እንዲናገሩ ያደረጓቸው አምባሳደር ተሾመ ናቸው፡፡ ሰው መመስገን ያለበት ሲሞት ብቻ መሆን የለበትም፡፡ አምባሳደር ተሾመ የሰለጠነ አስተሳሰብ ያላቸው፣ የዲፕሎማሲ ጥበብን የተካኑ፣ ስለፓርላማ ምንነት ብቻ ሳይሆን ስለአሰራሩም የጠለቀ ግንዛቤ ያላቸው፣ እያንዳንዷን ሰነድ አንብበው ወደ ስብሰባ የሚመጡ ጥንቁቅ ፖለቲከኛ መሆናቸውን በአምስት ዓመት ቆይታዬ አስተውያለሁ፡፡ አምባሳደር ተሾመ 547

ባህሪ፣ 547 ፍላጎት፣ 547 አመለካከት፣… ያላቸውን የምክር ቤት አባላት አቻችለው በመምራት ለመድብለ ፓርቲ አሰራር ባዶ የነበረውን ፓርላማ በሰነድ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት እንዲኖረው ያደረጉ ሰው ናቸው፡፡

በአንድ ፓርቲ ስም ተወዳድረው የተመረጡ የምክር ቤት አባላት ምክር ቤት ከገቡ በኋላ ፓርያቸውን ቢለቁም መቀመጫቸው ባስመረጣቸው ፓርቲ ስም እንዲሆን በምክር ቤቱ ደንብ ላይ የተደነገገ በመሆኑ የኢዴአፓ-መድህን አባል የነበሩት እነ አቶ ተመስገን ዘውዴ መቀመጫ አልነበራቸውም፡፡ እናም አምባሳደር ተሾመ በሕግ መሰረት መብትና ጥቅሙ ሊከበርለት የሚገባውን እያከበሩ፣ ለሌሎች ደግሞ ከተጨባጭ ሁኔታው በመነሳት መፍትሄ (Pragmatic Solution) እንዲኖር ባያደርጉ ኖሮ እነ አቶ ተመስገን የምክር ቤቱን መቀመጫ አሙቆ ከመሄድ የዘለለ ሚና አይኖራቸውም ነበር፡፡

ተቃዋሚዎች በተትረፈረፈ ሰዓት አንድ ደቂቃ፣ ሁለት ደቂቃ ተሰጠን የሚል አቤቱታ እንደሚያሰሙት ሁሉ፤ የኢህአዴግ አባላት ደግሞ ‘አፈ-ጉባዔው የኢህአዴግን ሰዓት ለተቃዋሚዎች እየሰጠ ምክር ቤቱን ፋይዳ ያለው ሃሳብ ማቅረብ የማይችሉ ጥራዝ ነጠቅ ተቃዋሚዎች መፈንጫ አደረገው፣ በራሳችን ሰዓት አሰደበን’ ወዘተ. ይሏቸው እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

ከዚህ ሌላ ስለ አምባሳደር ተሾመ መናገር የሚገባኝ ነገር አለ፡፡ በምክር ቤቱ ደንብ መሰረት አፈ-ጉባዔው ገለልተኛ መሆን የሚጠበቅበት ስብሰባዎችን በሚመራበት ወቅት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ አምባሳደር ተሾመ ግን ይህንን ቢያውቁም በብዙ አጋጣሚዎች የሁሉም የምክር ቤት አባላት አፈ-ጉባዔ መሆናቸውን ለማሳየት ሲጥሩ አስተውያለሁ፡፡ ለምሣሌ፤ አቶ ተመስገን ዘውዴ እና አቶ ገብሩ ገ/ማሪያም ታመው በውጪ ሀገር እንዲታከሙ የገንዘብ መዋጮ ማሰባሰብ ባስፈለገበት ወቅት አምባሳደር ተሾመ በምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ የመጀመሪያውን ፊርማ ከማኖራቸውም በላይ ሌሎች የኮሚቴው አባላትም እንዲያዋጡ አርአያነት ያለው ተግባር መፈጸማቸውን አይቻለሁ፡፡

እናም፣ አምባሳደር ተሾመ ሁሉንም አቻችለው ምክር ቤቱን መምራታቸውን በበኩሌ በአድናቆት ነው የማየው፡፡ ስለሆነም፣ አምባሳደር ተሾመ የእነ አቶ ተመስገን ባለውለታ ናቸው እንጂ በክፋት መንፈስ ስማቸው መነሳት የሚገባቸው ሰው አይመስሉኝም፡፡ በሌላ በኩል፣ በአምባሳደር ተሾመ ቦታ አቶ ተመስገን ቢሆኑ ኖሮ የስንት የምክር ቤት አባላት አፍንጫ በቦክስ ሊሰበር እንደሚችል የአቶ ተመስገንን መጽሐፍ ያነበበ ሁሉ ሊረዳው የሚችል ይመስለኛል፡፡

አቶ ተመስገን ሌላው ስለእኔ የተናገሩት ውሸት በመጽሐፉ በገጽ 184 ላይ የተጠቀሰው ነው፡፡ እንዲህ ይላል “**በዕለቱ… ለፓርላማ ‘አልሸባብ የተባለው አክራሪና ጂሃዲስት ቡድን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥል… ግልጽ የሆነ አደጋ ተከስቷል፡፡ ስለዚህ የተከበረው ፓርላማ ወታደር እንድናስገባ ድጋፍ እንዲሰጠን እንጠይቃለን’ የሚል ጥያቄ መጣ፡፡ … በቅድሚያ ለዚህ ጉዳይ በመሽቀዳደም መርቆ ‘ግቡ እንጂ’ ያላቸው … አቶ አብዱራህማን ነበር**” ይላሉ አቶ ተመስገን፡፡

እዚህ ሃሳብ ውስጥ ሁለት ውሸቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፤ በዚህ አጀንዳ ላይ በእለቱ ኢዴፓን በመወከል የተናገረው አቶ ልደቱ ነበር እንጂ እኔ አልነበርኩም፡፡ አቶ ተመስገን እኔን ለመወንጀል ባላቸው የተቻኮለ መንፈስ የውር የድንብር ሳይጓዙ ረጋ ቢሉ ኖሮ አቶ

ልደቱ በእለቱ ያቀረበው ሃሳብ ከአቶ መለስ ጋር ያጋጨው እንደነበር ማስታወስ ይችሉ ነበር፡፡ ዳሩ ምን ያደርጋል ጥላቻ አውሯቸዋል! በዚያ አጀንዳ ዙሪያ አቶ ልደቱ ሃሳቡን ሲያቀርብ **"በደርግ ዘመን ኢህአፓና ሕወሓት ከሶማሊያ መንግስት ጋር አብረው ነበር..."** በማለቱ አቶ መለስ በሰጡት መልስ **"አቶ ልደቱ አንተ ያኔ ልጅ ስለነበርክ አታውቀውም"** የሚል መንፈስ ያለው መልስ መስጠታቸውን በወቅቱ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ስርጭትን የተከታተለ ሁሉ የሚያስታውሰው ይመስለኛል፡፡ እናም እኔ በዚያ ጉዳይ ላይ አልተናገርኩም፤ አቶ ተመስገን ሆን ብለው በመዋሸት የመጽሐፉን አዘጋጅም አንባቢንም አሳስተዋል፡፡

የአቶ ተመስገን ሌላው ውሸት፣ ነገር ያሳመርኩ መስሏቸው **"በቅድሚያ ለዚህ ጉዳይ በመሽቀዳደም መርቆ 'ግቡ እንጂ' ያላቸው..."** የሚለው አገላለጽ ነው፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው በፓርላማው አሰራር የተናጋሪዎች ስም ዝርዝር ቀድሞ ለአፈ-ጉባዔው ስለሚሰጥ፣ በስብሰባ አዳራሹ ውስጥ እጅ እያወጡና እየተሽቀዳደሙ መናገር አይቻልም፡፡ አቶ ልደቱም ቢሆን ተሽቀዳድሞ አልተናገረም፡፡ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ኢዴፓ ሦስተኛ ተናጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ስለሆነም ይህ የአቶ ተመስገን ውሸት መታረም አለበት፡፡

በአቶ ተመስገን መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ነገሮች በተደጋጋሚ ተጠቅሰው አስተውያለሁ፡፡ የእርሳቸውን ተደባዳቢነት፣ ጀግንነት እና የሌሎችን ፈሪነትና የሰውነት መንቀጥቀጥ፡፡ ተደባዳቢነታቸውን በምክር ቤት ቆይታየ አይቻለሁ፣ ሰምቻለሁም፡፡ በእኔ ላይ ሁለት ጊዜ ሊፈጽሙት ነበር፡፡ እንግሊዝ ሀገር በሄድንበት ወቅት ከአቶ ሽፈራው ጃርሶ ጋር ለመደባደብ ሲጋበዙም አይቻለሁ፡፡ አቶ አየለ ጫሚሶ ጋር ተደባደቡ ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ እርግጠኛ ባልሆንም ከአቶ መሐመድ አሊ ጋርም ግብግብ ገጥመው ነበር ሲባልም ሰምቻለሁ፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከፓርላማው በስተጀርባ የነበረው የአቶ ተመስገን "ዴሞክራሲያዊ" እንቅስቃሴ እንግዲህ ይሄ ነው!!! በእኔ እምነት አቶ ተመስገን መግባት የነበረባቸው ፓርላማ ሳይሆን ቦክስ ፌዴሬሽን ነው፡፡ እዚያ የሚፈልጉትን ዓይነት ቡጢ ቢፈልጉ በአማተር፣ ቢያሻቸው በፕሮፌሽናል ደረጃ ማግኘት ይችሉ ነበር፡፡ ግን እኛው ራሳችን በሰራነው ስህተት ከመርካቶ ጎትተን አምጥተን፣ ፖለቲከኛ አደረግናቸው፣ ፓርላማም አስገባናቸው፡፡ ይኸው በመጽሐፍ ጭምር በውሸት ስማችንን እያጠፉ ወረታውን እየከፈሉን ነው፡፡ ሁሉንም ሕዝብ ይፍረደው!!!

ወደ ሌላው የአቶ ተመስገን ውሸት እናምራ፡፡ አቶ ተመስገን በጥር ወር 1997 ዓ.ም የኢዴፓ አባል መሆናቸውን በገጽ 119 ላይ ይነግሩናል፡፡ በገጽ 121 ላይ ደግሞ "የኢዴፓን ፎርም ከሞላሁ ከሦስት ወር በኋላ [ከሦስት ወር በኋላ ማለት ከሚያዝያ 1997 በኋላ ማለት ነው] አዲስ የመተባበር ወሬ ተሰማ... ቅንጅት የሚባል ፓርቲ በአራት ፓርቲዎች አማካይነት ሊመሰረት እንደሆነ ይፋ ሆነ" ይላሉ አቶ ተመስገን፡፡ ይህንን ብለው ቢያቆሙም ጥሩ ነበር፡፡ ቀጥለው ደግሞ "በጥቅምት ወር 1997 ዓ.ም ... ቅንጅት ተመስርቶ ይፋ ሆነ" በማለት ሐራምባና ቆቦ የሚረግጥ ሃሳብ ያስነብቡናል፡፡ አቶ ተመስገን በአግባቡ መዋሸቱንም አልቻሉበት!

አቶ ተመስገን "እኔ የኢዴፓ አባል ከሆንኩ ከሦስት ወር በኋላ ቅንጅት ተመሰረተ" የሚለውን ሃሳብ ያቀረቡት "ቅንጅትን በመመስረቱ ሂደት እኔም ነበርኩበት" ለማለት ይመስለኛል፡፡ ይሄ ደግሞ ተራ የታሪክ ሽሚያ ነው፡፡ ነገር ግን ሀቅ ምንጊዜም ስለሚያንቅ ሁለት መስመር ሳይራመዱ ቅንጅት እርሳቸው የፓርቲ አባል ከመሆናቸው በፊት መመስረቱን እየተናነቃቸው ነግሩናል፡፡ እንዲህ ያለውን የአቶ ተመስገንን እዚያና እዚህ

የሚረግጥ መያዣ መጨበጫ የሌለው ሃሳብ ሳነብ በአእምሮዬ የተጉላላው “አቶ ተመስገን በሌሎቹ የመጽሐፉ ገፆች የተናገሯቸው ሃሳቦች ምን ያህል ተዓማኒ ናቸው?” የሚል ጥያቄ ነው፡፡ አሁንም ፍርዱን ለአንባቢ እተዋለሁ!

ሌላው አቶ ተመስገን እኔን በተመለከተ ያነሱት ሃሳብ፤ እኔ በሀገር ጉዳይ ላይ የምቀልድ “ባንዳ” መሆኔን ለማስረዳት ያቀረቡት ምሣሌ ነው፡፡ እንዲህ ይላሉ “**የፓርላማ ጓደኞቼ እነማን እንደነበሩ ለማሳየት አንድ ግለሰብ ጠቅሼ ብናገር ደስ ይለኛል… ግለሰቡ አብዱራህማን ይባላል… በአንድ የአማካሪ ም/ቤት ስብሰባ ላይ ‘የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አልሸባብን በአንድ ሳምንት ድል መታ’ ሲባል… በፍጥነት ‘የተከበሩ አፈ-ጉባዔ እባክዎ ሁኔታዎችን ያመቻቹልንና የመከላከያ ሰራዊቱን ግማሽ መንገድ ሄደን እንድንቀበለው ያድርጉ’ አለ**” ይሉኛል፡፡

አቶ ተመስገን ይህንን ሃሳብ ያቀረቡት እኔን “ባንዳ” እና ከሀዲ አድርጎ ለማሳየት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አቶ ተመስገን “ባንዳ” የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም የገባቸው አልመሰለኝም፡፡ ሁላችንም እንደምንገነዘበው “ባንዳ” ማለት የሀገር ጠላት ጋር በማበር ሀገርን የሚወጋ፣ መረጃ የሚያቀብል፣ ለጠላት የሚሰልል፣… በአጭር አነጋገር የእናት ጡት ነካሽ ማለት ነው፡፡ ታዲያ በዚያ ወቅት የባንዳና የከሀዲነት ሚና የነበረው እኔ ነኝ ወይስ እነ አቶ ተመስገን? እንዲያው ለነገሩ እንዲዘምት እውቅና የሰጠነው ሰራዊት የጀግና ስራ ሰርቶ፣ አሸንፎ ሲመጣ የጀግና አቀባበል እንዲደረግለት ሃሳብ ማቅረብስ ምኑ ላይ ነው ሀጢያቱ?

እኔም ሆንኩ ፓርቲዬ ኢዴፓ የኢትዮጵያ ሰራዊት ወደ ሶማሊያ ገብቶ በሀገራችን ላይ ያንዣበበውን ግልጽና ወቅታዊ አደጋ (Clear and Present Danger) ይመክት፣ ያምክን ብለን ስንወስን፤ እነ አቶ ተመስገን ይህንን በመቃወም የባንዳ አቋም ያዙ፡፡ ድል ያደረገው ሰራዊት በድል ሲመለስ የጀግና አቀባበል ይደረግለት ሲባል ደግሞ ይህንንም እንደ ክህደት ቆጠሩት፡፡ ከባንዳ ተግባር ጋር አመሳሰሉትና አረፉት! እንዲህ ያለ የተወናገረ፣ እጅና እግር የሌለው ሃሳብ ከጤናማ አእምሮ የሚመነጭ አይመስለኝም፡፡ ለማንኛውም በሀገሪቱ ጉዳይ የባንዳነት ሚናን ሲያራምድ የነበረው ማን እንደሆነ ታሪክና ሕዝብ ይፍረደው!

አቶ ተመስገን ከእኔ ሌላ ስሙን ጠቅሰው የዘለፉት አቶ አሊ አበጋዝን ነው፡፡ አቶ አሊ አበጋዝን ደግሞ “ቀይ ሆኖ የቀለም ድርቀት የሚታይበት” (ገጽ 173) ይሉታል አቶ ተመስገን፡፡ ይህቺን የአቶ ተመስገንን አሽሙር ካነበብኩ በኋላ ከት ብዬ ነው የሳቅኩት፡፡ የሳቅኩት አቶ አሊ የቀለም ድርቀት የሚታይበት በመሆኑ ሳይሆን፤ የቀለም ድርቀቱ የተገላቢጦሽ መሆኑ ስለታየኝ ነው፡፡ ይህንን አባባሌን እንደሚከተለው ላስረዳ!

በዚህ አባባል አቶ ተመስገን እየነገሩን ያለው አቶ አሊ ያልተማረ፣ ያልተመራመረ፣ እውቀት ያነሰው፣… መሆኑን ነው፡፡ እኔ እንደማስታውሰው አቶ አሊ ፓርላማ ሲገባ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዲፕሎማ ተመርቆ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እነ አቶ ተመስገን በየድራፍት ቤቱ በሃሜት ሲቆዝሙ አቶ አሊ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በኢዱኬሽን የትምህርት መስክ በቢ.ኤ ዲግሪ፣ እረፍት ሳይወስድ ትምህርቱን ቀጥሎ በዚያው ሙያ በማስተርስ ዲግሪ ተመርቆ ነው ወደ ሀገሩ የተመለሰው፡፡

አቶ ተመስገንስ? አቶ ተመስገን 8ኛ ክፍልን ሳውላ ጨርሰው ኮሜርስ ገቡ፡፡ ከኮሜርስ በሴክሬታሪ ታይፒስትነት ተመረቁ፡፡ (ያኔ ኮሜርስ በሰርተፊኬት ነበር የሚያስመርቀው) እዚያው ኮሜርስ ጥቂት አስተማሩና አሜሪካ ሄዱ፡፡ አሜሪካ ሄደው “ተርኪ” የተባለ ወፍ

ስጋ መበለታቸውንና መጥበሳቸውን እንጂ ከየትኛው ዩኒቨርሲቲ፣ በምን የትምህርት መስክ እንደተመረቁ በመጽሐፋቸው ውስጥ አንድም ቦታ ላይ አልተናገሩም፡፡

እናም ሃያ ሁለት ዓመት በአሜሪካን ሀገር የተርኪ ሥጋ እየጠበሰ፣ ማክዶናልድ ሲገምጥ የኖረ ሁሉ በእውቀት የተጥለቀለቀ፣ የበቃና የነቃ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ባለመሆኑ፤ አቶ ተመስገን የት ዩኒቨርሲቲ፣ በምን የትምህርት መስክ፣ ምን ዓይነት ዲግሪ (ቢ.ኤ ወይም ማስተርስ ዲግሪ)፣ እንዳላቸውና በመቼ ዓመተ ምህረት እንደተመረቁ ሳይደብቁ ይንገሩን፡፡ ይህንን ከነገሩን ቀሪውን "ነግል" አድርገን "የቀለም ቀንድ" መሆንዎን እናረጋግጣለን፡፡ ካለበለዚያ የቀለም ድርቀቱ የተገላቢጦሽ መሆኑ እርግጥ ይሆናል፡፡

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ለአቶ አሊ አበጋዝ ደውየለት "አቶ ተመስገን በአንድ ጣቱ ወደ እኔ ሲያመለክት አራቱ ጣቶች ወደ እሱ ማነጣጠራቸውን ልብ አላለውም፡፡ የኔ የትምህርት ሪከርድ እዚያው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለለት፡፡ ሂዶ ማረጋገጥ ይችላል፡፡ የእርሱ ማስረጃ ግን ፓርላማ ባለው ማህደሩ እንኳ የለም፡፡ ያኔ ሁሉም የፓርላማ አባል የትምህርት ማስረጃውን ለፓርላማው ጽ/ቤት እንዲያቀርብ ታዞ ሲያቀርብ አቶ ተመስገን አላቀረበም፡፡ ለምን? ስለሌለው! ከዚህ በላይ የቀለም ድርቀት የትም አይገኝም፡፡ አቶ ተመስገን ማስተርስ ዲግሪ አለኝ እያለ በጨበጣ ከመፎከር ማስጃ ያቅርብ፡፡ አለበለዚያ 'ይሉኝን ባልሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ፣ ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል' የሚለውን እንተርትበታለን" ነበር ያለኝ፡፡

አቶ ተመስገን የአቶ አሊን ተረትና ምሳሌ ማቅረብም ካላዋቂነት ጋር አያይዘው ተችተዋል፡፡ አበው ሲተርቱ ግን 'ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ' ይሉ ነበር፡፡ ታዲያ የአቶ አሊ ጥፋት ምኑ ላይ ነው? እውነቱን እንነጋገር ከተባለ እስከ አሁን ድረስ ከአእምሮዬ ጓዳ የማይለዩት የአቶ አሊ "አዙረሽ እዩው ቢኳት አዙራ ለበሰቺው፣ ሞኝ አሳላፊ ወንድሙን ያልፋል" የሚሉት ዓይነት ተረትና ምሳሌዎች እንጂ የአቶ ተመስገን የኬኔዥያን የኢኮኖሚ ፍልስፍናዎች አደሉም፡፡

አቶ ተመስገን በመጽሐፋቸው ውስጥ በተደጋጋሚ ስማችንን በመጥቀስ "ከሀዲ፣ ባንዳ፣..." እያሉ የሚወነጅሉት በዋናነት እኔንና አቶ አሊ አበጋዝን ነው፡፡ የከብት ሌባ፣ የቢላዎ ቀበኛ፣ ሴት ደፋሪ፣ ገንዘብ አጭበርባሪ፣... ወዘተ. የፓርላማ አባል በነበረበት ሁኔታ ከምኑም ከምኑም የሌለነውን እኔን እና አቶ አሊ አበጋዝን የሌለ ሀጢያት እየፈበረኩ የሚለጥፉብን ለምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ እውነተኛውን ምላሽ የሚያውቁት አቶ ተመስገንና አላህ ብቻ መሆናቸውን እገነዘባለሁ፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ ግን የኛ "ሀጢያት" የእስልምና እምነት ተከታይ እና የወሎ ክፍለ ሀገር ተወላጅ መሆናችን ነው፡፡ ይህንን ያልኩበት ምክንያት፤ በአቶ ተመስገን ደምና አጥንት ውስጥ ለዘመናት የኖረው የፊውዳል አስተሳሰብና የነፍጠኛነት ስሜት አምጦ የወለደው "የእስላሞ ፎቢያ" መንፈስ የለም ብሎ ለመደምደምም አስቸጋሪ ስለሆነ ነው፡፡

እኔም ሆንኩ አቶ አሊ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የምንከተለውን ሃይማኖትም ሆነ የምንወለድበትን ስፍራ ወደንና መርጠን ያደረግነው አደለም፡፡ ለነገሩ አሁንም ደግመህ ተወለድ ብባል በበኩሌ ከወሎ ውጪ ምርጫ ሊኖረኝ አይችልም፡፡ ወሎ በብዙ ነገሯ የኢትዮጵያ ሞዴል ናትና!! እዚህ ላይ ለአቶ ተመስገን አንድ ነገር ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ ክቡር ሆይ! ልክ እንደርስዎ ሁሉ እኛም የራሳችን እምነትና አስተሳሰብ አለን፡፡ የእርስዎ

እምነት፣ ነፃነትና አስተሳሰብ እንዲከበርልዎ እንደሚፈልጉት ሁሉ የእኛም እምነት፣ ነፃነትና አስተሳሰብ ሊከበርልን ይገባል፡፡

አቶ ተመስገን እኔን ብቻ አደለም የሚጠሉት፡፡ በአምስት ዓመት የፓርላማ ቆይታየ ኢ.ዴ.ፓንም እንማይወዱ አስተውያለሁ፡፡ ፖለቲከኛ ደግሞ በውስጡ ጥላቻ የሰነቀ እለት ነው የመጨረሻውን ሞት ‘ሞተ’ የሚባለው፡፡ መጥላትም ከነበረባቸው ሃሳብን እንጂ የሃሳቡን ባለቤት መሆን አልነበረበትም፡፡ የእኛ ሀገር ፖቲከኞች ትልቁ ጉድለት ይህንን አለመለየታቸው ነው፡፡ አቶ ተመስገን እኔንስ “ፖለቲካ ያስተማርንህ እኛ ነን” አልከኝ ብለው ጠሉኝ፡፡ አቶ ተመስገንን ለፓርላማ አባልነት ያበቃቸው፣ ዛሬ ላገኙት ታዋቂነት ያበቃቸው፣ የሕይወት ታሪካቸውን የያዘ መጽሐፍ ጭምር ለማሳተም መሰረት የሆናቸውን (ፖለቲከኛ ባይሆኑ ኖሮ የአቶ ተመስገን ታሪክ የተርኪ ሥጋ መበለት ነበር፡፡ እሱ ደግሞ መሸጥ የሚችል መጽሐፍ አይሆንም ነበር) ኢ.ዴ.ፓን ለምን እንደሚጠሉት አይገባኝም፡፡ ኢ.ዴ.ፓ የአቶ ተመስገን ባለውለታ እንጂ ደመኛ ጠላታቸው እንዴት ሊሆን ይችላል?

እስቲ የኢ.ዴ.ፓ እና የእርስዎን ተመሳሳይ እርምጃዎች እንመልከት፡፡ ኢ.ዴ.ፓ እንደ ድርጅት በቅንጅት ላይ የወሰደው እርምጃ እርስዎ በግልዎ ከወሰዱት እርምጃ የተለየ አደለም፡፡ ለምየሣሌ፤ እርስዎ በግልዎ (ከኢ.ዴ.ፓም ቀድመው) ህዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም ፓርላማ ገቡ፡፡ ኢ.ዴ.ፓም እንደ ድርጅት ታህሳስ 27 ቀን 1998 ዓ.ም ወስኖ ፓርላማ ገባ፡፡ እርስዎ በሚያምኑበት ጉዳይ ላይ አቋም ይዘው በፓርላማ ይከራከሩ ነበር፡፡ ኢ.ዴ.ፓም በሚያምንበት ጉዳይ ላይ አቋም ይዞ በአባላቱ አማካይነት ይከራከር ነበር፡፡ ኢ.ዴ.ፓ የሊበራል ዴሞክራሲን የሚከተል መሆኑን በይፋ ይናገራል፡፡ እርስዎም እንዲሁ ይላሉ፡፡ እርስዎ የቅንጅት አመራሮች በወቅቱ የወሰዱትን እርምጃ አይደግፉም ነበር፡፡ ኢ.ዴ.ፓም አይደግፍም ነበር፡፡ የቅንጅት አመራሮች ስህተት እንደሰሩ ኢ.ዴ.ፓ ያምናል፡፡ እርስዎም ያምናሉ፡፡ በዚህ ዓይነት በርካታ ምሣሌዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለናሙና ያህል ይኸው ይበቃል፡፡

ታዲያ በእርስዎና በኢ.ዴ.ፓ መካከል ያለው የጎላ ልዩነት ምንድነው? እናስ ከኢ.ዴ.ፓ የለየዎት የትኛው የተጣረሰ መርህ ነው? እስከ አሁን ድረስ ሊገባኝ ያልቻለው ይህ ነው፡፡ አቶ ተመስገን ፖለቲካ የገባቸው፣ የመርህ ሰው ቢሆኑ ኖሮ በፓርቲው ውስጥ ስህተት ካለ የውስጥ ትግል እያደረጉ አብረው ይሰሩ ነበር እንጂ ኢ.ዴ.ፓን አይለቁም ነበር፡፡ የሚፈልጉትን የፓርቲ መሪነትም ቢሆን ኢ.ዴ.ፓ የሚነፍግዎ አይመስለኝም፡፡ አቶ ተመስገን ግን ፖለቲካም አልገባቸው፣ የመርህ ሰውም አደሉም፡፡

አቋም ያለው የመርህ ሰው የአንድ ፓርቲ አባል ሆኖ የሚዘልቀው እዚያ ፓርቲ ውስጥ በሕብረተሰቡ **“የሚወደድ”** ወይም **“የሚጠላ”** ሰው ስላለ አደለም፡፡ ለሕዝብ ሊሸጥ የሚችል የጠራ ዓላማ፣ ግልጽ የሆነ ፖሊሲ፣ መርህና የአሰራር ስርዓት ያለው መሆኑ ነው ለአንድ የፖለቲካ ሰው የሚያስፈልገው፡፡ በሂደት መጥራት ቢገባቸውም ኢ.ዴ.ፓ ደግሞ እነዚህ ነገሮች አነሰም አደገ ነበሩት፡፡ የውስጥ ትግል እንደሆነ በየትኛውም ፓርቲ ውስጥ ምንጊዜም ይኖራል፡፡ እንዲያውም የውስጥ ትግል የሌለው ፓርቲ የሞተ ፓርቲ ነው የሚባል፡፡

በገጽ 124 እና 125 ላይ የመጽሐፉ አዘጋጅ “በ1997 ዓ.ም የምርጫ ወቅት የታየው የሕዝብ ተነሳሽነት… ዴሞክራሲን የማምጣት ትግል በአንደኛነት የማን ነው?” በማለት ላቀረበው ጥያቄ አቶ ተመስገን የሰጡት ምላሽ በሳቅ የሚያፈነዳ ነው፡፡ “እንዴ! ሕዝቡ ነዋ!” ነበር ያሉት፡፡ አቶ ተመስገን ፖለቲካን የማወቅ ችግር ብቻ አደለም ያለባቸው፤ የተነገራቸውንም

በአግባቡ የመገንዘብ ችግር አለባቸው፡፡ ያ ባይሆን ኖሮ እንደዚያ ዓይነት መልስ አይሰጡም ነበር፡፡

በመሰረቱ ሕዝብ ለመብት፣ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የሚደረግን ትግል ይደግፋል እንጂ ቀጥተኛ የመሪነት ሚና አይኖረውም፡፡ ሊኖረውም አይገባም፡፡ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደት የሕዝብና የፓርቲ ሚና የተለያዩ ናቸው፡፡ የሕዝቡ ሚና የፖለቲካ ፓርቲዎች በጠሩት ስብሰባ ላይ በመገኘት ድጋፉን ወይም ተቃውሞውን ማሳየት፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣ በመራጭነትና በታዛቢነት መሳተፍ፣... ወዘተ. ዋነኛ ተግባራቱ ሲሆኑ፤ የህዝቡን ፍላጎቶች የሚያንጸባርቁ ዋና ዋና አጀንዳዎችን በመቅረጽ የትግሉ ግንባር ቀደም መሪዎች መሆን ያለባቸው ፓርቲዎች ናቸው፡፡ ፓርቲዎች ደግሞ በፓርቲ አመራር አካላትና እንደየአግባቡ በግለሰቦች ይወከላሉ፡፡

መሪ የሌለው ማህበረሰብ (ሕዝብ) መንጋ ነው፡፡ መንጋ ያለ መሪ ከተንቀሳቀሰ የጥፋት ኃይል ነው የሚሆን፡፡ ልክ እንደ ጎርፍ ያገኘውን ይጠርጋል፡፡ መንጋ በስሜት እየተመመ ሲሄድ ያገኘውን "ነበዝ" ድንገት አንስቶ ሽኮኮ በማለት "ማንዴላ! ማንዴላ!" ከማለት የማይመለስ፣ መደማመጥ የማይችል፣ ተረጋግቶ ማሰብ የማይችል የውድመት ኃይል ነው፡፡ ለዚህም ነው ፈረንጆቹ "Mobe has no brain. It is a damaging force" (በመንጋ የሚተም [ሕዝብ] አእምሮ የለውም፡፡ የጥፋት ኃይል ነው) የሚሉት፡፡ እናም ይህንን ኃይል አስክኖ መምራት የሚችል መሪ (Leader) ያስፈልጋል፡፡ በኔ እምነት የ1997ቱ ምርጫ ውጤት አልባ ሆኖ የተቋጨው በከፊል "ሕዝቡ" በከፊል ጋዜጦች ከፊት ለፊት ሆነው፤ "የፖለቲካ መሪዎቹ" ከኋላ በመሆናቸው ይመስለኛል፡፡ በአግባቡ ያልተደራጀ እና መሪ (Leader) የሌለው ማህበረሰብ እንዲህ ያለ እጣ ፈንታ ሊገጥመው መቻሉ ደግሞ አዲስ ነገር አደለም፡፡ ለማንኛውም እንዲህ ያለውን ሰፊ ጥናትና ምርምር የሚያስልገው ጉዳይ በተመለከተ በእውቀት ላይ ያልተመሰረተ የተጣደፈ አስተያየት ከመስጠት መታቀቡ የተሻለ ይመስለኛል፡፡ ሙያንም የሚጠይቀ ጉዳይ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቻችን በዚህ ረገድ የታዩ ድክመቶችን ለመፈተሽ ተግተው መስራት ይጠበቅባቸዋል ባይ ነኝ፡፡ ካለበለዚያ ስሜትን ከመግለጽ የዘለለ፣ ትርጉም ያለው፣ ሁላችንንም ሊያስማማ የማይችል ደመነፍሳዊ መልስ ነው የሚሆን፡፡

በአቶ ተመስገን መጽሐፍ ውስጥ በርካታ እርስ በርሳቸው የሚዋቁ ሃሳቦችን አንብቤአለሁ፡፡ አቶ ተመስገን ጠንካራ ሰራተኛ ነኝ ብለው ይከራከራሉ፡፡ ይህንንም በመጽሀፉ ውስጥ በተደጋጋሚ ገልጸውታል፡፡ እኔ ግን የእርሳቸውን ደካማነትና ተደጋጋሚ ውድቀት ነው ያስተዋልኩት፡፡ በመጽሐፉ ላይ እንዳስተዋልኩት የአቶ ተመስገን የውድቀት ታሪክ ከሳውላ ወደ አዲስ አበባ ከመጡበት ጊዜ ይጀምራል፡፡ አቶ ተመስገን ኮሜርስ ትምህርታቸውን ጨርሰው እዚያው አስማሪ ሆኑ፡፡ (ገጽ 33) ነገር ግን ከገጽ 36-37 እንደተገለጸው ጠጪና ቁንጆ አሳዳጅ በመሆናቸው ጥሩ ደመወዝ ቢኖራቸውም ከአያታቸው ተበድረው መኪና የገዙበትን ገንዘብ እንኳ መክፈል አልቻሉም - ውድቀት! ለትምህርት አሜሪካ ቢሄዱም ምን እንደተማሩና ምን ውጤት እንዳገኙ አይታወቅም - ውድቀት! አሜሪካን ሀገር በሰሩበት አንድ ኩባንያ አንድ አሜሪካዊ አለቃቸው "በአሜሪካ የሰዎች ስራ የሚለካው በውጤታማነትና በብቃት" (ገጽ 78) መሆኑን ነግሮ አባረራቸው - ውድቀት! ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ የንግድ ድርጅቶችን ማቋቋማቸውንና ይሁን እንጂ የንግድ አሰራሩን ማጣጣም ስላልቻሉ (ገጽ 104) ከስረው መዝጋታቸውን ይነግሩናል - ውድቀት! ከአቶ አየለ ጫሚሶ ጋር ቅንጅትን ከመሰረቱ በኋላ ተስማምተውና ተግባብተው መስራት ባለመቻላቸው ተባረሩ (ገጽ 189-190) - ውድቀት! ማስተማር አልቻሉም፣ ተቀጥረው መስራትም አልቻሉም (ገጽ 274) - ውድቀት! ለዚህ ሁሉ ውድቀታቸው ደግሞ መንስኤው ስርዓቱ ነው ብለው ያምናሉ (ገጽ 275) - ሌላ ውድቀት!

ከዚሁ ጋር ተያይዞ እኔን የገረመኝ ነገር አቶ ተመስገን ከንግድ ስራቸው ከስረው ከወጡ በኋላ (ገጽ 104 - 105) በአድማስ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ፈጠራ (Entreprenuership) ትምህርት ማስተማር መጀመራቸው ነው፡፡ ለራሳቸው ያልተሳካላቸውን የንግድ ስራ ፈጠራ ለሌሎች እንዴት ሊያስተምሩ እንደቻሉ እንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ፡፡

በአጠቃላይ፤ የአቶ ተመስገንን የሕይወት ታሪክ ከያዘው መጽሐፍ ለመረዳት እንደቻልኩት የአቶ ተመስገን ታሪክ የስኬት ሳይሆን የውድቀት ታሪክ ነው፡፡ ከሌሎች ውድቀት ትምህርት ሊገኝ እንደሚችል ቢታመንም፤ ትምህርቱ በበጎነት የሚወሰድ አይሆንም፡፡ እናም የመጽሐፉ መታተም ጊዜ፣ ጉልበትና ሃብት ከማባከን የዘለለ ሀገራዊ ፋይዳ ይኖረዋል የሚል እምነት የለኝም፡፡

ሌላው የአቶ ተመስገን መጽሐፍ ያረጋገጠልኝ ጉዳይ አቶ ተመስገን እኔ ያልኩት ብቻ መሆን አለበት የሚሉ ግትር፣ አምባገነን፣ ከእርሳቸው አስተሳሰብ ውጪ አመለካከት ያለውን በጉልበት ጭምር ከማጥፋት የማይመለሱ ጨካኝ መሆናቸውን ነው፡፡ አምባገነኖች፣ ጨካኞችና ግትሮች ደግሞ የዴሞክራሲ አዋላጆች፣ የልማት አርበኞች፣ የሕዝብ አለኝታዎች ሆነው አያውቁም፡፡ ዴሞክራሲንም ሀገርንም አያሳድጉም፡፡ እናም አቶ ተመስገን የሚሻላቸው ከፖለቲካው ሙሉ ለሙሉ ወጥተው ቢራቸውን እየለጉ መቆዘም ብቻ ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡